oref.org.il

# በአስቸኳይ/አደገኛ ሁኔታ ጊዜ የሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች

የሲቪል
አስተዳደር
በሃላፊነት
ይመራል



መስከረም 2012

# ማዉጫ


ምቅደም ____ ገጽ 3

የመሸሸጊያ ክፍል እንዴት መምረጥ አለብን ____ ገጽ 4



የመከላከያ ክልሎች ካርታ ____ ገጽ 5

የማስጠንቀቂያ ደዉል ሲሰማ የሚደረግ የመከላከያ መመሪያዎች _ ገጽ 6

ለመሸሸጊያ ክፍል የሚያስፈልጉ እቃዎች ____ ገጽ 7



ቤተሰብ እንዴት መዘጋጀት አለበት ____ ገጽ 8 - 12



የአደገኛ ንጥረ ነገሮች መመሪያ ____ ገጽ 13

የመሬት መንቀጥቀጥ ሲደርስ መደረግ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች __ ገጽ 14 - 15


የሲቪል አስተዳደር በሃላፊነት ይመራል

# ለአስቸኳይ/አደገኛ ሁኔታ ጊዜ ዝግጁ ሆኖ መቆየት አስፈላጊነቱ ምንድን ነዉ?

ቀደም ሲል በዓለም ላይ እና በሀገራችል ላይ በተከሰቱት ነገሮች ላይ የተዉሰደዉ ተለምዶ እንደሚያመለክተው አደጋዎችና አስቸኳይ ነገሮች ሳይታሰቢና ማስጠንቀቂያ ሳይሰጡ ለከሰቱ እንደሚችሉ ነው። ነገር ግን ለእንደዚህ ዓይነት ነገሮች አስቀድሞ ለተዘጋጀና መደረግ ያለበትን ጠንቅቆ ያወቀ እራሱንና ቤተሰቡን ከአደጋ ያድናል።

**መቋቋም የሚያስፈልጉን ነገሮች ከወዲሁ የታወቁ ናቸው። መቋቋሙም የራሳችን ሃህል ነው።**

የሲቪል አስተዳደር ወይም “ ፒኩድ ሃኦሬፍ “ በአደጋ ጊዜ ቀድሞ በመድረስ እርዳታ ከሚሰጡ ድርጅቶች፣ ከመንግስት መ/ቤቶች፣ ከከተማ አስተዳዳሪዎች እንዲሁም ህዝብን ለመርዳት በበጎ አድራጊነት አገልግሎት ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር በመሆን አደጋ በሚደርስበት ጊዜ በአንድ ላይ እርዳታ ለመስጠት ተዘጋጅተዉ ይገኛሉ። ሆኖም ግን የህዝቡ አስቀድሞ መዘጋጀት፣በመመሪያዉ መሰረት በአደጋ ጊዜ መደረግ ያለበትን ጠንቅቆ ያወቀና በበጎ አድራጎትነት እርስ በርሱ ከተረዳዳ ለብዙ ጊዜ አብረን መቋቋም እንችላለን።



# 1 የመሸሸጊያ ክፍሎችን እንደ ማስ ጠንቀቂያዉ ደወል የጊዜ ብቃት መጠን ይምረጡ

የሲቪል አስተዳደር በሃላፊነት ይመራል

## የመሸሸጊያ ክፍሎችን እንዴት መምረጥ እንችላለን?

የመሸሸጊያ ክፍሎ በቤት ዉስጥ ወይም በማንኛዉም የመጠለያ ቦታ እንዲሆን ለመወሰን የሚከተሉትን ደረጃዎች በመከተል ይሆናል፤

**የሕንጻ ውስጥ የመሸሸጊያ ክፍል** (ד"ממ) ወይም **የፎቅ ላይ መሸሸጊያ ክፍል** (ק"ממ)

ከምትኖሩበት ህንጻ ከቤት ዉስጥ ወይም በህንጻዉ ዉስጥ የመሸሸጊያ ክፍሎች ከለሉ በጣም ጥቂት ውጫዊ ግድግዳዎች፣ መስኮቶችና ክፍተቶች ያሉበትን የመሸሸጊያ ክፍል መምረጥ ያስፈልጋል። ከመሸሸጊያ ክፍል ዉስጥ በሚገኙት መስኮቶች ላይ የወረቀቱ ዉፍረት 100 ሚክሮን በሆነ ስስ ወረቀት ማጣበቅ ወይም የተሰባበሩ መስታዉቶች እንዳይበታተኑ የሚረዳ ማጣበቂያ መስኮቱ ላ ማጣበቅ ያስፈልጋል። (እነዚህን ነገሮች ለቤት መስሪያ የሚያገለግሉ እቃዎች መሸጫ ሱቅ ዉስጥ ማግኘት ይቻላል) ከላይ የተጠቀሱት ዓይነት የመሸሸጊያ ቦታዎች ከለሉም የፎቁን ደረጃዎች እንደመሸሸጊያ ክፍል መምረጥ ይቻላል።

ቤታቸዉ ከሦስተኛ ፎቅ በላይ የሆኑና የሕንጻ/የቤት ውስጥ የመሸሸጊያ ክፍል (ד"ממ) የሌላቸዉ ከቤታቸዉ ሁለት ፎቆች መዉረድ አለባቸው። ህንጻዉ ባለሦስት ፎቅ ብቻ ሁኖ ሦስተኛዉ ፎቅ ላይ የሚገኙ ንዋሪዎች የቤት ዉስጥ መሸሸጊያ ክፍል የሌላቸዉ ደግሞ አንድ ፎቅ መዉረድ አለባቸው።


**ሚክላጥ (የጋራ የሆነ መሸሸጊያ ክፍል)** - የማስጠንቀቂያ ደወል እንደተሰማ በተወሰነልን ባጭር ጊዜ ዉስጥ መድረስ የሚቻል ከሆነ።

## የመከላከያ ክልሎች ካርታ

ካርታዉ ላይ እንደተጠቀሰዉ ለስቪል አስተዳደር (ፒኩድ ሃኦሬፍ) አዲስ የኡኦኑ የማስጠንቀቂያ መስጫ ደዉሎች አለዉ በነዚህ የማስጠንቀቂያ መስጫ ደዉሎች ለተለያዩ ከተሞች እንደየክልላቸዉና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ገደባቸዉ መጠን የማስጠንቀቂያ ደወል ያሰማል።

“የማስጠንቀቂያ ጊዜ” ይህ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ሮኬቶች ተተኩሰዉ እስኩወድቁ ድረስ ባለዉ ጊዜ ዉስጥ መሸሸጊያ ክፍል እንድንገባ ያለን የስዓት ገደብ ነው። ይህ የማስጠንቀቂያ ደወልም የሚሰማዉ ሮኬቶች ወይም ሚሳኤሎች ይወድቃሉ ተብለዉ ወደታሰቡበት ክልሎች ብቻ ነዉ። ተጨማሪ ማስጠንቀቂያና መመሪያዎች በቴሌቪዥን እና በራዲዮ በኩል ይተላለፋል። በመከላከያ ክልሎች ካርታ ላይም እያንዳንዱ ክልል ወደ መሸሸጊያ ክፍል ለመድረስ ያለዉ የጊዜ ገደብ ተጠቅሷል እዛ ላይም መመልከት ይችላሉ።

### የሀገሪቱ የመከላከያ ክልሎች ካርታ






# 1 የመሸሸጊያ ክፍሎችን እንደ ማስ ጠንቀቂያዉ ደወል የጊዜ ብቃት መጠን ይምረጡ

## የሲቪል አስተዳደር በሃላፊነት ይመራል

## የማስጠንቀቂያ ደወል ሲሰማ የሚደረጉ መመሪያዎች

የማስጠንቀቂያ ደወል ወይም የፈንጅ ድምጽ በተሰማ ጊዜ ወደ መሸሸጊያ ክፍል ባለን የጊዜ ገደብ ዉስጥ ለመግባት የሚቀጥሉትን መመሪያዎች በመከተል ይሆናል፤

- በሕንጻ ውስጥ ያሉ ፡ በፍጥነት ወደ ሕንጻው መሸሸጊያ ክፍል (ፕ"ዐዐ) ግቡና የብረቱን መስኮት ዝጉ። በሕንጻው ውስጥ የመሸሸጊያ ክፍል (ፕ"ዐዐ) ከሌለ በጣም ጥቂት ውጫዊ ግድግዳዎች፣ መስኮቶችና ክፍተቶች ወዳሉበት ክፍል መግባት ያስፈልጋል። የዚህ ዓይነት ክፍል ከሌለ ወደሕንጻው ደረጃዎች ወጥቶ መቀመጥ ያስፈልጋል። በሕንጻው መሸሸጊያ ክፍል (ፕ"ዐዐ) ወለል ላይ ከመስኮቱ በታች ተቀመጡ። ከመስኮቱ ፊት ለፊት አትቀመጡ።
- ከሕንጻ ውጪ የምትገኙ ከሆነ ፡ ወደሕንጻው ወይም ሌላ በአቅራብኢያው ወደሚገኝ መሸሸጊያ ግቡ። ሜዳ ላይ ከሆናችሁ - መሬት ላይ ተጋደሙና ራሳችሁ እንዳይጐዳ/እንዳይመታ በእጃችሁ ሸፍናችሁ ያዙት።
- በተሽከርካሪ/በመኪና ለምትጓዙ ፡ መንገድ ዳር ተሽከርካሪውን ካቆማችሁ በኋላ በአካባቢው ሕንጻ ወይም መሸሸጊያ ቦታ ካለ ወደዚያ ግቡ። ከመኪናው ውስጥ ባለን የጊዜ ገደብ ዉስጥ በአካባቢው ሕንጻ ወይም መሸሸጊያ ቦታ መድረስ የማይቻል ከሆነ መኪናውን በመንገድ ዳር በማቆም መሬት ላይ ተጋደሙና ራሳችሁ እንዳይጐዳ/እንዳይመታ በእጃችሁ ሸፍናችሁ ያዙት።
- ከ10 ደቂቃዎች በኋላ ፡ ተጨማሪ የማስጠንቀቂያ ድምጽ ወይም ሌላ መመሪያ እስካልተሰጠ ድረስ ከመሸሸጊያው ክፍል መውጣት ይቻላል።
- ሮኬቶች በወደቁበት ቦታ ላይ አትሰባሰቡ። እንደዚሁም ወድቆ ከሚገኝ ሮኬት እንዲሁም ከሌሎች አጠራጣሪና ወድቀው ከሚገኙ ነገሮች ራቁ። የዚህ ዓይነት ክስተተ ካጋጠመ ጉዳዩን ለፖሊስ ደውሎ ማስታወቅ ያስፈልጋል።



# 2 የመሸሸጊያ ክፍሎችን አዘጋጁ

## ለመሸሸጊያ ክፍል የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች

ባለን የሥዓት ገደብ ለመድረስ የሚያመቸንን የመሸሸጊያ ክፍል ከመረጥን በኋላ የሚያስፈልገንን የዕቃ ዓይነቶች ወደ ክፍሉ ለማስገባት በሚቀጥለዉ ቅደም ተከተል መሰረት መሆን አለበት፤

- ማስክ (ጭንብል)
- አንዳንድ መመሪያዎችን ለመስማት/ለመከታተል እንዲረዳን እንደ ኮንፒዩተር፣ ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ ከነባትሪዉ የመሳሰሉ ሜዲያዎች
- ከተጨማሪ ባትሪ ድንጋይ ጋር ባትሪ
- በቆርቆሮ የታሸጉ ምግቦች፤ የሚቆረጠሙ
- ለእያንዳንዱ ሰዉ ለሦስት ቀን የሚበቃ 4 ሊትር የታሸገ ዉሃ
- የእጅ ስልክ፣ የባትሪ መሙያና ተጨማሪ ባትሪ
- አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ ወረቀቶች (የህክምና ወረቀቶች፣አስፈላጊ የሆኑ የግል መረጃዎች እንዲሁም የባልክ ወረቀቶች)
- የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ
- በአደጋ ጊዜ የሚደርሱ ድርጅቶች፣የቤተሰብና የጎረቤት የስልክ ቁጠር ዝርዝሮች
- ጊዜዉ በቀላሉና በጥሩ ሁኔታ እንዲያልፍ የሚረዱ እንደ መጫወቻ ጋዜጦች የመሳሰሉ
- ቀዳዳዎችን ለማሸግ የሚረዱ እቃዎች ( ከፖሊኤትሊን የተሰራ ዉፍረቱ 100 ሚክሮን የሆነ ላስቲክና ማጣበቂያ ሥስ ባለ 30 ሚክሮን እንዲሁም 50 ሚሊ ሜትር የሆነ ሰፊ የማጣበቂያ ወረቀት)
- የግል ዕቃ መያዣ ፖርሳ - እንደአጋጣሚ ሁኖ ለተወሰኑ ቀናቶች ከቤት መራቅ ካለብን መያዝ የሚያስፈልገን ነገሮች ( ለምሳሌ፤ መድሃኒቶች፣ ብር፣ ድንኳን፣ ተጨማሪ ልብሶች፣ ክብሪቶች፣ ሻማዎች፣ ለብዙ ጉዳዮች የሚያገለግል ቢላዋ፣ ለህጻናት የሚያስፈልጉ ነገሮች፣ ልዩ እንክብካቤ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች የሚሆን መሳሪያ ወዘት)

# 3 ቤተሰባችሁን አዘጋጁ

የሲቪል አስተዳደር በሃላፊነት ይመራል

የእለት እለት ንሯችን አንዳንድ ጊዜ በሚደርሱ የደጋ ሁኔታዎች ሊተግውጎሉ ይችላሉ።

አስቸኳይ/አደጋ ነገሮች አብዛኛዉን ጊዜ የሚደርሱት ሳይታሰቡ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጡ ስለሆኦነ ባስቸኳይ ነገሮችን እንድንቋቋምና ሂወታችን እንድናድን ያደርጉናል። የሰዉ ልጅ በፈተና ጊዜ እንደችሎታዉና እንደልምዱ ነገሮችን ይቋቋማል። አደጋ በሚደርስበት ጊዜ አዲስ መልስ ለማግኘት መሞከር ዋጋ የለዉም። በአደጋ ጊዜ በፍጥነት ብዙም ሳናስብበት ወዲያዉ ምላሽ እንሰጣለን። ስለዚህ ረጋ ባልን ወቅት ለማሰብ፣ ለመማር፣ ልምድ ለመዉሰድና ለመዘጋጀት ጊዜ ይኖረናል።

ለአንድ ግለሰብ ብቻ የሚደርስ የአደጋ አይነቶኦች አሉ ለምሳሌ ያክል፤ የመኪና አደጋ ወይም ቃጠሎ። ሌላዉ ደግሞ ብህብረተሰብ ላይ የሚደርሱ አደጋዎች አሉ ለምሳሌ፤ የመሬት መንቀጥቀጥ ወይም ህዝብን የሚጎዳ ጦርነት የመሳሰሉት።

ሙሉ በሙሉ አደጋዎችን ልናስቆማቸዉ አንችልም ሆኖም ግን በሰዉ ላ የሚያመጡትን የጉዳት መጠን ልንቀንስ እንችላለን። በዓለማችን ላይ በተገኘዉ ልምድ መሰረት የአደጋዉን ሁኔታና የሚያመጣዉን ችድር አስቀድመዉ የተረዱ ሰቆች ከአደጋዉ እራሳቸዉን እና አብረዋቸዉ ያሉትን ለማዳን ችለዋል።

አደጋ በሰፊዉ ህብረተሰብ የደረሰ ጊዜ የመጀመሪያ እርዳታ ለተጎዳዉ ህዝብ የሚደርሱ ድርጅቶችና ይህዝብ ደህንነት ድርጅቶች ባስቸኳይ ላይደርሱ ይችላሉ ስላዚህ እኛ ለመቋቋም መደራጀትና ማወቅ አለብን።

አስቀድሞ ለነገሮች ሁሉ መዘጋጀት ከሂወታችን ጋር አብሮ የሚሄድ ነገር ነዉ። አንዳንድ ቤተሰቦች ለተለያዩ ነገሮች ዝግጁ ይሆናሉ ለምሳሌ ወደዉጭ ሃገር ለመሄድ፣ ለወሊድ፣ ለዉትድርና እንዲሁም አደጋ በሚደርስበት ጊዜ ዝግጁ መሆን አለባቸዉ።

በአደጋ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ በአንድ ላይ አደጋዉን መቋቋም አለበት። በዚህ ጊዜ አብሮ በመተባበር በጋራ በመስራት፣ አንዱ ላብዱ ተስፋ በመስጠት እና ቅድሙያ ዝግጅት በማድረግ አደጋዉን መቋቋም ይቻላል።

## አንድ ቤተሰብ በአደጋ ጊዜ ማድረግ ያለበት ዝግጅት ለ3 የከፈላሉ

የተለምዶ ጊዜ፣ የዝግጅት ጊዜ፣ አደጋዉ በሚደርስበት ጊዜ
እነኝህ ዝግጅቶች በአዘቦት ጊዝዘ በአደጋ ጊዜም ይረዱናል።

### በተለምዶ (በአዘቦት) ጊዜ

ለቤተሰብ የሚረዱ የአደጋ ጊዜ ዝግጅቶች በአራት መንገዶች ይመደባሉ፤

→ 1 ምን ዓይነት የአደጋ አይነቶች ሊደርሱባችሁ እንደሚችሉ ማወቅ።
ምን ዓይነት የአደጋ አይነቶች በአካባቢያችሁ ሊደርሱ እንደሚችሉ
ለይቶ ማወቅ።
አንዳንድ መረጃዎች ማሰባሰብ።

→ 2 ከቤተሰባችሁ ጋር አብሮ በመወያየት ለቤተሰብ የሚረዱ ቅድመ ዝግጅቶች ማዉጣት።
የተለያዩ ዉይይቶች በማድረግ በአደጋ ጊዜ ለሚደረጉ ነገሮች እቅድ ማዉጣት።

→ 3 እቅዱን ሥራ ላይ አዉሉት
- ቀደም ሲል ያወጣችሁትን እቅድ ተግባር ላይ አውሉት ( የጎደለ ነገር ካለ ግዙ፣ የመሸሸጊያ ክፍሉን አዘጋጁ) ።
- በአደጋ ጊዜ ጭንቀትና ዉጥረትን ለመቋቋም የሚረዱ ነገሮችን ግዙ ( በዚህ ጊዜ መቋቋም እንድትችሉ የሚረዳችሁን እውቀቶችና መንገዶች እወቁ) ።

→ 4 ለአደጋ ተብሎ የታቀደዉን ቅድመ ዝግጅት መተደጋጋሚ ማጤን መለማመድና አዳዲስ እቅዶች ካስፈለገ መጨመር።
በየጊዜዉ ከቤተሰብ ጋር ዉይይት ማድረግ፣ ጊዜን በመጠቀም - በሌላ ክልል አደጋ መድረሱን ከሰማችሁ ይህ ነገርም ወዳላችሁበት ክልል ሊደርስ እንደሚችል ከታወቀ እኛ ላይ ደርሶ ቢሆን ምን ማድረግ ነበረብን በማለት መወያየትና የሚያስፈልጉ ነገሮች ባካባቢዉ እንዲገኙ ማድረግ።

# 3 ቤተሰባችሁን አዘጋጁ




## ለአደጋ ጊዜ የሚረዱ የቤተ ሰብ ዝግጅቶች

ለወላጅና ልልጆች ዋና ድጋፍ ቤተሰብ ነዉ ስለዚህ የቤተሰብ አባል በሙሉ በዝግጅቱ ዉስጥ ተሳታፊ ይሁኑ በዚህም ምክንያት የተለያዩ ልምዶችን በመዉሰድ ችግሮችን ሊቋቋሙ ይችላሉ፡፡

## የቤተሰብ ዉይይት

- የቤተሰብ ዉይይት የሚካሄደዉ በሁለት መንገድ ነዉ፤ ተልዕኮና ስሜታዊ፡፡ የተልዕኮ መንገድ - ቤተሰቡ የዛቻዉን ምንነትና አስፈላጊዉን ምላሽ ካወቀ በከፍተኛ ደረጃ ዝግጁ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡ ስሜታዊዉ መንገድ - ቤተሰቡ የሚደርስባቸዉን ስሜታዊ ሁኔታ ከተረዱ በኋላ የእርስ በርስ መተጋገዝ ሁኔታን መፍጠር፡፡
- የዉይይቲ ባህሪ መሆን የሚገባዉ እንደተሳታፊዉ የቤተሰብ አባል መሆን አለበት፡፡ የቤተሰቡን አባልት ልዩ ፀባይ ግምት ዉስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ የአባላቱን እድሜ፣ ከህፃናት ልጆች ጋር ዉይይት ማድረግ ( በቲአትር መልክ ሁኔታዉን አስመስሎ ማሳየት፣ በወላጆች መመሪያ መሰረት አጠር ያለ ዉይይት ማድረግ) ከትልልቅ ልጆች ጋር ግን ዉይይቱ ከወላጆች ጋር ሰፋ ባለ መልኩ መወያየት ያስፈልጋል፡
- ዉይይቱን ለማድረግ አመቺ ጊዜ መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ ምግብ በሚመገቡበት ጊዜ ወይም ቴሌቪዥን በሚመለከቱበት ጊዜ መሆን የለበትም፡፡ ስለ ሌላ አስቸኳይ ጉዳይ በሚያስቡበት ጊዜ እና ከጥል በኋላ ወይም በጭንቀት ጊዜ ዉይይቱን ማካሄድ አያስፈልግም፡፡

## ልጆች በአደጋ ጊዜ ጥያቄዎች ይጠይቃሉ

ልጆች ባስቸኳይ/በአደጋ ጊዜ ጥያቄዎች ይጠይቃሉ ራሳቸዉ የሚጎዱበትን ለራሳቸዉ ስለሚደርስባቸዉ ጉዳትና ሞት የጠይቃሉ፡፡ ስለሚደርሰዉ አደጋ ልጆች ዩኦናል ብለዉ ከሚያስቡት መልስ ይልቅ ስለሚደርሰዉ አደጋ ግልጽ መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ትክክል ካልሆነ ሃሳብ መዋዥቅ ከእዉነቱ ይልቅ አስፈሪ ይሆናል፡፡ የወላጆች መልስ እንደልጁ የእድሜ መጠንን ብስለት መሆን አለበት፡፡

**በዚህ የሥራ ሂደት ጊዜ ወላጆች ልጆቻቸውን በመምራት ረገድ ታላቅ ሚና አላቸው፡፡ በአንድ በኩል ግልጽ ላልሆኑ የሕይወት ድርጊቶች ማብራሪያ መስጠት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ኃላፊነትን በመውሰድ አደጋ እንዳይደርስበት መከላከል፣ በተለይም ራሱ ሊቋቋማቸው በማይችላቸው ነገሮች የጥፋተኝነት ስሜት እንዳይሰማው ማድረግ ናቸው፡፡**

## በቤተሰብ ዉስጥ የክፍፍል ሥራ

| አከናዋኝ | የሥራ ድርሻ | |
|---|---|---|
| | በአደጋ ጊዜ ጉዳት ሊያደርሱ በሚችሉ ነገሮች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ | ባዘቦት ጊዜ |
| | በአደጋ ጊዜ ከክልሉ ለመራቅ እንዲቻል ሻንጣ ማዘጋጀት ዉጭ መዉጣት በማይቻልበት ጊዜ የሚረዱ ነገሮችን ማዘጋጀት | |
| | የቃጠሎ የመሬት መንቀጥቀጥና የሮኬት ትኮሳ ጊዜ ህዝብን ከክልሉ ማራቅ ያስመስሉ ልምምድ ማድረግ | |
| | ለቤተሰቡ አባል በሙሉ ማስክ (ጭንብል) መኖሩን ማረጋገጥ ከለለም ከማከፋፈያ ቦታዉ ሂዶ ማምጣት | |
| | ለአደጋ ጊዜ የሚያስፈልጉ የስልክ ቁጥር ዝርዝር ማዘጋጀት | |
| | በአደጋ ጊዜ የቤት እንስሳዎችን ምን ማድረግ እንዳለብን ማቀድ | |
| | ለአደጋ ጊዜ የሚያስፈልጉ ነገሮች በሙሉ መኖራቸዉን ማረጋገጥ | በዝግጅት ጊዜ |
| | ሊመጣ ስለሚችለዉ አደጋ የሚደረገዉን ቅድመ ዝግጅት ልምምድ ማድረግ | |
| | ራዲዮ/ቴሌቪዥን መመክፈት የሚሰጠዉን መመሪያ መስማት | በአደጋ ጊዜ |
| | ልህዝብ ደህንነት ሃይል ደዉሎ መጥራት | |
| | የቤተሰቡ አባል በሙሉ የት እንዳኩ ማረጋገጥ | |
| | ለአደጋ ጊዜ የተዘጋጀዉን ሻንጣ መዉሰድ | |
| | ለጎረቤቶች እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸዉ መጠየቅ | |
| | አደጋ በደረሰበት ጊዜ ወይም ከዚያ በኋላ ለአያቶችና ለቅርብ ዘመዶች በመደወል ደህንነታቸዉን መጠየቅ | |
| | ለአደጋ ጊዜ የሚረዱ የቤተሰብ ዝግጅቶች ማደስ | ወደ አዘቦት ኑሮ መመለስ |

# 3 ቤተሰባችሁን አዘጋጁ

የሲቪል አስተዳደር በሃላፊነት ይመራል

## ግንኙነትን ማጥበቅ

ከቤተሰብ አባላት ጋር ወይም ከሚቀርቡን ሌሎች ሰዎች ገር በአደጋ ጊዜ እንዴት ግንኙነት መፍጠር እንደሚቻል ማወቅ ብውጣም አስፈላጊ ነው።

## ሰንጠረዡን አሟልታችሁ በግልጽ ከሚታይ ቦታ ለጥፉት

| ስም | የቤት/የሥራ ስልክ ቁጥር | የእጅ ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|
| አባት | | |
| እናት | | |
| እህት/ወንድም | | |
| እህት/ወንድም | | |
| አያት | | |
| አያት | | |
| ጎረቤት/ጓደኛ | | |

## በተለያዩ የአደጋ ጊዜዎች ለመጠየቅ የሚያስፈልጉን ድርጅቶች

| ድርጅት | ስልክ ቁጥር | ድረ ገጽ |
|---|---|---|
| ፖሊስ ጣብያ | 100 | www.police.gov.il |
| ማጌን ዳቪድ አዶም | 101 | www.mdais.org |
| እሳት አደጋ | 102 | www.102.co.il |
| የሲቪል አስተዳደር (ፒኩድ ሃኦሬፍ) | 1207 | www.oref.org.il |
| በከተማው የሚገኝ ያስቸኳይ ክፍል | 106/107/108 | |
| መብራት ሃይል | 103 | www.isreal-electric.co.il |

# ሌሎች ተከሳች ነገሮች

## የከሚካል/መርዝ ሚሳኤል በሚተኮስበት ጊዜ ምን ማድረግ ያስፈልጋል

የከሚካል/መርዝ ሚሳኤሎች ዛቻ ሲኖር የሲቪል አስተዳደር (ፒኩድ ሃኦሬፍ) ስለ ክፍል ማሸግ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎች እና ስለ " ኤርካት ማጌን" አጠቃቀም መግለጫ ለህዝቡ ይሰጣል።

## የአደገኛ ንጥረ ነገሮች መመሪያ

### አደገኛ ንጥረ ነገሮች ምንድን ናቸው?

አደገኛ ንጥረ ነገር ማለት ለሰዉ ልጅ፣ ለጤንነት እና ለአካባቢ ጎጂ የሆነ ነግር የያዘ ማለት ነዉ። ይህ አደገኛ ንጥረ ነገር ከተበታተነ በመርዝነት፣ በልብለሻና ቃጠሎ በመሳሰሉ መንገዶች ይጎዳል። የአደገኛ ንጥረ ነገር ሁኔታዎች በአካባቢ ልዩነቶች የተነሳ ሊከሰት ይችላል፤ የቴክኒክ ብልሽት፣ አድጋ፣ የተፈትሮ ጉዳት፣ በጦርነት በመሳሰሉት። በጦርነት መልክ ለሚደርሱት ነገሮች በሙሉ የሲቪል አስተዳደር (ፒኩድ ሃኦሬፍ) ተዘጋጅቶበታል።

### አደገኛ ንጥረ ነገሮች የት ነዉ የሚገኙት?

ብዙዎች የአደገኛ ንጥረ ነገሮች የሚገኙት ከሚካል ፋብሪካዎች ሲሆን እንዲሁም በተለያዩ ፋብሪካዎች ይገኛሉ። የአደገኛ ንጥረ ነገሮች ቦታ የሚገኘዉ በተለይ ሃገሪቱ ላይ በተለያዩ የፋብሪካ አካባቢዎች ሲሆን አደገኛ ንጥረ ነገሮች ከቦታ ቦታ የሚተላለፉትም በባቡርና በጭነት መኪና ነው።

### በአደገኛ ንጥረ ነገሮች እንዳንጎዳ ምን ማድረግ አለብን?

በቤቱ ዉስጥ በሚገኝ የመስኮትና የክፈተት ነገሮች አንስተኛ በሁነበት ክፍል ዉስጥ ዘግቶ መቀመጥ። ልዩ አደጋ በደረሰ ጊዜ ምናልባት ከአካባቢዉ ለማራቅ መመሪያ ያሰጣል። ባጠቃላይ ግን በዜና ማሰራጫ መሳሪያዎች በኩል ስለሚሰጠዉ ተጨማሪ መመሪያ ማዳመጥ።



የሲቪል አስተዳደር በሃላፊነት ይመራል

# የመሬት መንቀጥቀጥ ሲደርስ መደረግ የሚገባቸዉ ነገሮች

**ካሁን በፊት ባካባቢያችን አጥፊ የሆነ የመሬት መንቀጥቀጦች ደርሰዋል፤ የጊዜ ጉዳ ነው እንጅ ሌላ ሃይለኛ የሆነ የመሬት መንቀጥቀጥ እንደሚደርስም የታመነ ነው። ዛሬ ብንዘጋጅ ሂወት እናድናለን።**

## ቤትንና የሥራ ቦታን ማዘጋጀት

- ሳጥኖችን፣ መደርደሪያዎችንና ማዘጋኖችን በግድግዳ ላይ በደንብ አጣብቁ።በደርደሪያዎችን ከአልጋ በልስይ አትስድርጉ።
- ለአደጋ ጊዜ የሚሆን ምግብና ዉሃ፣ የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ፣ራዲዮና በባትሪ የሚሰራ መብራት አዘጋጁ። አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንም መጠበቅ ያስፈልጋል።
- ከላይ በተጠቀሰዉ መመሪያ መሰረት አስቀድማችሁ እቤትም ሆነ ሥራ ቦታ በመሬት መንቀጥቀጥ ጊዜ የምትሄዱበት ቦታ አዘጋጁ።
- በቤቱ ዉስጥ የሚገኙትን የመብራት፣ የዉሃና የጋዝ መዝጊያዎችን እወቁ።
- መኪና ዉስጥ የሚቀመጥ ለአደጋ ጊዜ የሚያስፈልግ ሻንጣ አዘጋጁ።

## ሕንጻ ውስጥ በምትሆኑ ጊዜ

የመሬት መንቀጥቀጥ በሚጀምርበት ጊዜ ሕንጻ ውስጥ የምትገኙ ከሆነ በሚከተሉት ቅደም ተከተል መሰረት ባስቸኳይ ወደመጠለያ ቦታ እለፎ፤

1. ባጭር ሰከንዶች ዉስጥ ከህንጻዉ ዉስጥ መዉጣት የሚቻል ከሆነ ወደ ክፍት ወደሆነ ቦታ ዉስጥ እለፉ። (በተለይ አንድ ፎቅ ብቻ ወይም ምድር ቤት ዉስጥ ለምትገኙ)።
2. ባስቸኳይ ከህንጻዉ ዉስጥ መዉጣት የማትችሉ ከሆነ መሸሸጊያ ክፍል ዉስጥ (ፓ"ממ) ግቡ። የመሸሸጊያ ክፍል በር ከፍት ማስቀረት ያስፈልጋል።
3. ባስቸኳይ ከህንጻዉ ዉስጥ መዉጣት የማይቻል ከሆነና መሸሸጊያ ክፍል (ፓ"ממ) ከለለ ወደሕንጻው ደረጃ ክፍል ወጡ ከተቻለም ወደመዉጫዉ በር ለመድረስ መሄዳችሁን ቀጥሉ።
4. ከላይ የተጠቀሱትን ማድርግ የማትችሉ ከሁነ ከከባድ እቃ ስር ተቀመጡ ወይም ወደግድግዳ በመጠጋት መሬት ላይ ተቀመጡ።

ተጨማሪ መመሪያዋች፤

1. ህንጻዉን ክመልቀቃችሁ በፊት የጋዝና የመብራቱን ዋና መከፈቻና መዝጊያዎች ዝጉ።
2. ወደ መጠለያ/መከላከያ ቦታ በምታልፉበት ጊዜ ከግድግዳዎቭ፣ከመሶቶችና ከመደርደሪያዎች ራቁ።
3. በመሬት መንቀጥቀጥ ጊዜ በሊፍት መጠቀም የለም፤ ሊፍቱ ዉስጥ ተይዛችሁ ልትቀሩ ትችላላችሁና።
4. በተሽከርካሪ ወንበር ላይ ከተቀመጣችሁ ቆልፉችሁ ራሳችሁን በእጃችሁ ከልሉ (መጠለያ/መከላከያ ቦታ ከደረሳችሁ በኋላ)።

## ውጪ በምትሁኑበት ጊዜ፤

የመሬት መንቀጥቀጥ የሚደርሰዉ ከህንጻዉ ዉጭ እያላችሁ ከሆነ እዛዉ በመሆን ከህንጻዎች፣ ከድልድዮችና ከመብራት ሃይል እንጨቶች ራቁ።

## ወሃ ዳር በምትሁኑበት ጊዜ፤

የመሬት መንቀጥቀጥ በሚደርስበት ጊዜ ዉሃ ዳር ከሆናችሁ በማዕበል መጥለቅለቅ ቦታዉ እንዳይጥለቀለቅ አካባቢዉን ባስቸኳይ ልቀቁ። ቢያንስ በአንድ ኪሎሜትር ከዉሃዉ ዳር እርቁ። ከዉሃዉ ዳር ለመራቅ የማትችሉ ቢያንስ በአካባቢዉ ከሚገኘዉ 4 የፎቅ ህንጻ ላይ ዉጡ። የመሬት መንቀጥቀጥ ከደረሰ በኋላ ል 12 ሳዓቶች ያህል ወደ ባይር ዳሩ ክልል አትሂዱ።የዉሃዉ በህይልና በድንገት ወደኋላ መመለስ የሃይለኛ የመዐበል መጥለቅለቅ ምልክት ነው።

## ከመሬት መንቀጥቀጥ በኋላ መደረግ ያለባቸዉ ነገሮች፤

1. ከህንጽዉ በመዉጣት ወደ ክፍት ቦታ በማለፍ ከህንጻዎችና ከተቆራረጡ የኤሌክትሪክ ገመዶች ራቁ።
2. ለቤተሰቡ በአደጋ ጊዜ የሚያስፈልግ ሻንጣ ይዛችሁ ሂዱ፣፤
3. በዜና ማሰራጫ ለሚተላለፉ መመሪያዎች አዳምጡ።

## ከፈረሰዉ ህንጻ ሥር የሚገኙ፤

በአካባቢዉ በኩል ከፈረሰዉ ህንጻ ሥር የሚገኙ ሰዎች ካሉ በማመዛዘን እንሱን መኪናን ከፍ አድርጉ ብሚይዘዉ ምሳሪያ ወይም የብረት ምሰሶ በመጥቀም  ለማዉጥት ሞክሩ። የመጀመሪያ የህክምና እርዳታ በተቻለ መጠን ለማድረስ ሞክሩ።

## ተከታይ የመሬት መንቀጥቀጥ፤

ለተጨማሪ የመሬት መንቀጥቀጥ ዝግጁ ሁኑ - የ የሚሆነዉ የመሬት መንቀጥቀጥ ከደረሰ ከተወሰኑ ደቂቃዎች ወይም ከተወሰኑ ቀኖች በኋላ ነዉ ይህ መንቀጥቀጥም የተንቀሳቀሱ ህንጻዎችን ሊያፈርስ ይችላል። የሰዉ ሂወት ለማዳን ካልሆነ በቀር ከንደዚህ አይነት ሀንጻዎች ዉስጥ አትግቡ።

የሲቪል አስተዳደር በሃላፊነት ይመራል

## ለተጨማሪ መረጃ፤

www.oref.org.il

ለመረጃ ክፍል በስልክ ቁጥር 1207

የሲቪል አስተዳደር (ፒኩድ ሃዖሬፍ)